# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE SEVENTEEN: በእሳት መጫወት

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of scenes:**

**SCENE 1: ዳንኤል SNEAKS ምህረት OUT OF THE BOYS’ DORMITORY COMPOUND**

- ዳንኤል (M, 15)
- ምህረት (F, 15)
- በለጠ (M, 15)

**SCENE 2: ርዕሰ መምህርት ሰብለIN ዳንኤል 'S ROOM**

- ርዕሰ መምህርት ሰብለ(F, 50)
- በለጠ (M, 15)

**SCENE 3: ምህረት ARRIVES HOME**

- ምህረት (F, 15)
- አቶ ሙላቱ (M, 45)

**SCENE 4: ንጉሴ STEALS HIS FATHER’S CAR KEYS**

- ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)
- አቶ ጃለታ (M, )
- ንጉሴ (M, 15)

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርብላችሁ ድራማ ነዉ። በዚህ ድራማ ምህረት ፣ ንጉሴ እና ዳንኤል የሚባሉ ሶስት የቦንጎ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በየቀኑ የሚገጥማቸውን አስቸጋሪ የኑሮ ፍጥጫዎች ስንሰማ ቆይተናል። እስኪ ከእዚህ በፊት የተከሰተውን ጠቅለል አድርገን እናሰማችሁ።

ንጉሴ ብዙ ፈተናዎች ገጥመውታል። ታስታውሱ እንደው እናቱ ሌቦች አፍነው እና አስረዋቸው እንዲሁም ንብረታቸውን ዘርፈዋቸው ነው እቤቱ የደረሰው። ፖሊስም እስካሁን ወንጀለኞቹን በቁጥጥር ስር አላዋለም። ይህ በእንዲህ እንዳለ ንጉሴ ምህረትን ለማግኘት ያደረገው ጥረት አልተሳካለትም።

2. ምህረት (EP 12, 20): "ንጉሴ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ።

3. ንጉሴ : (...) "በጆሮዬ በልቤ በሁሉም ነገሬ እያዳመጥኩሽ ነኝ።

4. ምህረት : "ንጉሴ , እኔ...እኔ የምወደው"

5. ንጉሴ : "እኔም እወድሻለሁ ምህረት !"

6. ምህረት : "እንደሚመስለኝ እኔ የምወደው ዳንኤልን ነው። ይቅርታ አድርግልኝ ንጉሴ ."

እናም በስተመጨረሻ ምህረት ደጋግሞ ሲጠይቃት ለነበረው ከላቦሪያ ለመጣው የክፍል ጓደኛዋ ዳንኤል ወሰናለች። ይሁንና ግን ዳንኤል መውደዷን ስትገልፅለት በተግባር ካላረጋገጥሽልኝ ብሎ ወጥሮ ይዟት ነበር። እናም ስሜቷን እንድትገልፅለት እክፍሉ ድረስ እንድትመጣ ቢያደርግም ያቀደው ግን ድንገት ተደናቅፏል።

7. **ROMANTIC MUSIC**

8. **ዳንኤል (EPISODE 16, 78):**." ምህረት ነይ እጎኔ ተቀመጪ። እስካሁን ቆመሽ ነው ያለሽው። እስኪ እጅን ያዢኝ።

9. **(LINE 83) SFX: RAPID KNOCKING ON DOOR**

10. **በለጠ (86):** " በለጠ ነኝ። ቀይ ካርድ! ቀይ ካርድ!

11. **ምህረት (87):** "ቀይ ካርድ?ምን ማለቱ ነው?

12. **ዳንኤል (88):** " ቀይ ካርድ ማለት የትምህርት ቤት ኃላፊው እየመጡ ነው ለማለት እንደ ማስጠንቀቂያ የምንጠቀመው ነው። ቶሎ በይ ከዚህ በፍጥነት መውጣት አለብን።

በለጠ ርዕሰ መምህርቷ እየመጡ መሆናቸውን አሳውቋል። ግን ዳንኤል እና ምህረት በኃላፊዋ ከመያዛቸው በፊት ከክፍሉ ይወጡ ይሆን? እስኪ «በእሳት መጫወት» የተሰኘውን 17ኛ ክፍል እናድምጥ።

## SCENE ONE: ዳንኤል SNEAKS ምህረት OUT OF BOYS DORMITORY COMPOUND

13. **SFX: SCHOOL COMPOUND OUTSIDE**

14. **SFX: RUSTLING OF BUSHES**

15. ዳንኤል : **(in a hushed tone)** በጣም ይቅርታ ምህረት። የዛሬው ቀጠሮዋችን እንደዚህ ይቋረጣል ብዬ አላሰብኩም ነበር።

16. ምህረት: ምንም አይደል። ይገባኛል። **(concerned)** ግን ቁጥቋጦ ውስጥ መደበቁ አደገኛ አይደለም? እባብ ሊነድፈን እኮ ይችላል።…

17. **SFX: RUSTLING OF BUSHES**

**18.** ዳንኤል : ምንካሽ እንደዛማ መጥፎ ነገር አታስቢ። ይኸውልሽ። ልክ ይሄ ድብብቆሽ እንዳበቃ በለጠ ከዚያ ከመስኮቱ ላይ ሆኖ ምልዕክት ይሰጠናል። ከዚያም ወደ ክፍሌ ሄደን ካቆምንበት እንቀጥላለን።

**19.** ምህረት: **(shocked)** አይሆንም ዳንኤል ! እንደገና ወደእዛ አልመለስም። ርዕሰ መምህርት ሰብለ አንተ ክፍል እያለን እኛን ባለማግኘታቸው እድለኞች ነን። አሁን ወደቤት መሄድ ነው የምፈልገው። ይሄኔ እስካሁን መዘግየቴ አባቴን ግራ ሳያጋባው አይቀርም።

**20.** ዳንኤል : **(thinking hard)** ግን ምህረት ከእኔ ጋ እኮ ምንም ያህል ጊዜ አላሳለፍንም።

**21.** ምህረት : እንዴት እንደዚህ ትላለህ? አሁን እንኳን ካንተ ጋ ሆኜ ጊዜው እየበረረ እኮ ነው።

**22.** ዳንኤል : አዎ ግን... እ...ታውቂያለሽ...ማለቴ አሪፍ ጊዜ እንድናሳልፍ አንድ ነገር አሰቤ--

**KW BEGIN**

**23.** ምህረት: **(interrupts him)** ምን ለማድረግ ዳንኤል? እእእ?

**24.** ዳንኤል: ተቀራርበን ጥቂት ደስታ እንዲኖረን **(gets an idea)** የምልሽ ይገባሻል አይደል። እዚህ ማንም አያየንም። ቁጥቋጦው ሸፍኖናል። **(flirty voice)** እና... ምህረትዬ ትንሽ ብንጠጋጋ ምን ይመስልሻል?

**KW END**

**25.** ምህረት : ዳንኤል ... አልችልም። በጣም አዝናለሁ። ለእዚህ ዝግጁ አይደለሁም። በጣም አደገኛ ነው። እባክህ እንቆይ።

**26.** ዳንኤል **:** የምንቆየው ለምኑ ነው? ጊዜው አሁን ነው። ሰዓቱ አሁን ነው። እንደዚህ አይነት አጋጣሚ መልሰን ላናገኝ እንችላለን።

**27.** ምህረት **:** ሁለታችንም ይበልጥ አዋቂ እስክንሆን መጠበቅ አለብን። እንደውም እስከጋብቻችን ብንቆይ ይሻላል ብዬ አስባለሁ። እንደዚህ አይነት ነገር ከዚህ በፊት ፈፅሜ አላውቅም። ራሴን ለማገባው ሰው ላቆይለት እፈልጋለሁ።

**28.** ዳንኤል **:** **(acting emotionally hurt)** ስለዚህ ለእኔ ምንም ስሜት የለሽም ማለት ነው። ሁሉም ነገር በውሸት የተሞላ ነበር። ጥሩ አሁን ገባኝ። እኔ ደግሞ የምትወጂኝ መስሎኝ ነበር። …

**29.** ምህረት **:** **(confused)** ዳኒ በጣም ከባድ እያደረግሽብኝ ነው።መውደድ እወድሀለሁ። ይህንንም ታውቃለህ። ግን መቆየት ያለብን ይመስለኛል።

**30.** ዳንኤል **:** **(still acting hurt, putting her under pressure)** አትዋሽኝ ምህረት አትወጅኚም። ወደሺኝ ከሆነማ ጥቂት ፍቅር ታሳይኝ ነበር።

**31.** በለጠ **:** **(loud whistle from window, loud whisper)** ሄይ! መስመሩ ነፃ ሆኗል። አረንጓዴ መብራት። አትስጋ። በኔ ተወው።

**32.** ዳንኤል **:** **(cold)** ስለዚህ መስመሩ ነፃ ነው።አሁን የአጥሩን ሽቦ ወደ ላይ እይዝልሻለሁ። ተጠንቀቂ። አንዴ ከወጣሽ ግን ከወንዶች ግቢ ብቻ ሳይሆን ከት/ቤቱ ግቢ እና ከእኔም ህይወት ጭምር እንደምትወጪ እወቂ። **(bitterly)** ቻው ምህረት።

**33.** ምህረት**:** **(starts to cry)** ግን… ዳኒ … እባክህ። ነግሬህ የለም እንዴ…

**34. SFX: WIRE MESH BEING PULLED UP**

**35.** ዳንኤል **:** **(struggling to hold wire up)** ከዚህ በላይ ሽቦውን ወደ ላይ ይዤ መቆየት አልችልም።ምህረት።

**36.** ምህረት **:** **(sobs)** ደግና ሁን ዳንኤል ።

**37. SFX:** ምህረት **PASSING THROUGH SMALL GAP IN WIRE MESHED FENCE WHILE SOBBING**

**38. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE TWO:** ርዕሰ መምህርት ሰብለ**IN** ዳንኤል **'S ROOM**

**39. SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS IN DORM CORRIDOR**

**40. SFX: LOUD KNOCK ON DOOR**

**41.** በለጠ**:** **(responds from inside, pretending not to know who's behind the door)** እንዴ ዳኒ ? ከቤተ መፅሀፍት ተመልሰካል እንዴ?

**42. SFX: DOOR OPENS WITH CREAKING SOUND**

**43.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ**:** **(coldly polite)** ሰላም በለጠ ።

**44.** በለጠ**:** **(plays surprised)** ውይ ርዕሰ መምህርት ሰብለ! እንደምን ዋሉ? ይቅርታ በፍፁም እርሶ ይሆናሉ ብዬ አልጠበኩም ነበር። እኔ ደግሞ ዳንኤል የመጣ መስሎኝ ነበር።

**45.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ**:** እንደምን ዋልክ በለጠ ። በሩ ምን ነክቶት ነው? ዘይት መቀባት አለበት። ዳንኤል ክፍል ውስጥ ደግሞ ምን ትሰራለህ? ዳንኤል ካሳሁን የት ነው ያለው?

**46.** በለጠ : **(well-mannered)** ዳንኤል ቤተ መፅሀፍት ሄዶ ነው። ርዕሰ መምህርት ሊያጠና ፈልጎ ነው።

**47.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(firmly)** ሊያጠና ፈልጎ ነው? **(joking)** የሆነ ተዓምር እዚህ ትምህርት ቤት በየአጋጣሚው እንደተፈጠረ ነው፤ እሺበለጠ ! እንደተለመደው ክፍሎቻችሁን ለመፈተሽ ነው የመጣሁት። እንግዲህ ዳንኤል ከሌለ ዕቃዎቹን ልፈትሽ አልችልም። በል እስቲ አንተ ክፍል ውሰደኝ።

**48.** በለጠ: **(scared)** እ... እሺ...በሚገባ። ግን ክፍሌ ትንሽ እንደተዝረከረከ አስቀድሜ ልነግርዎ እወዳለሁ። ምናልባት እንዳፀዳው ትንሽ ደቂቃዎች ቢሰጡኝ?

**49.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(firmly)** አይሆንም ለዚህ ነው ቁጥጥሩን ባልታሰበ ጊዜ የምናደርገው ። ወደ ክፍልህ እንሂድ በለጠ። ምን ስታደርግ እንደነበር ማየት እፈልጋለሁ።

**50. SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS WALKING,** በለጠ **WALKING ALONGSIDE**

**KW BEGIN**

**51. SFX: ANOTHER DOOR IS OPENED**

**52.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(not so amused)** መልካም ወለሉ ላይ የተዝረከረኩትን የቆሸሹ ልብሶች እንዳላየ እሆናለሁ።

**53.** በለጠ : እሺ መምህርት። ይቅርታ አጥባቸዋለሁ ብዬ አስቤ ነበር።

**54.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: በል አሁን እቃዎችህን በሙሉ ከሻንጣው ውስጥ አውጥተህ አልጋህ ላይ እንድትዘረግፋቸው እፈልጋለሁ።

**55. SFX: PERSONAL BELONGINGS BEING EMPTIED ONTO BED**

56. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: በል አሁን እንደጅብራ ፊቴ አትገተር። (rummaging through things) እሺ. ምንም አዲስ ነገር የለውም። የትምህርት ቤቱን ህግ ከዚህ ቀደም ትጠብቅ እንደነበር አውቃለሁ።

57. በለጠ : አዎን መምህርት።

58. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምንድን ነው በለጠ እስቲ ተመልከት።እንዲህ መላቅጡ በጠፋው በተዝረከረከ ያልፀዳ ክፍል መኖር ምቾት ይሰጥሀል? ክፍልህን በሚገባ ማፅዳት አለብህ። ዳንኤል ከቤተ መፅሀፍት ሲመለስ ንገረኝ። መቼም ሁለታችሁም መጥፎ ነገር አታደርጉም። ልክ ነኝ?

59. በለጠ: (scared) አይደለም…ማለት አዎ አዎ ርዕሰ መምህርት

60. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: መልካም! እንግዲህ በዚሁ ቀጥሉ።

**KW END**

61. **SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS LEAVING**

62. **MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE THREE: ምህረት ARRIVES HOME</u>

63. **ATMO AT ምህረት 'S HOME LATE EVENING**

64. **SFX: DOOR SLOWLY OPENING**

65. አቶ ሙላቱ: (furious) ምህረት! ለምንድን ነው እንደዚህ ዘግይተሽ የመጣሽው? እስካሁን የት ቆይተሽ ነው?

66. ምህረት: (politely) እንዴት ነህ አባዬ? ይቅርታ አንድ ሰአት አርፍጄ በመምጣቴ…

67. አቶ ሙላቱ : (angry) ጥያቄ ያቀረብኩልሽ መሰለኝ ። የት ነበርሽ እስካሁን?

68. ምህረት : ከትዕግስት ጋ ቤተ መፅሀፍት ነበርን። ለፈተና እየተዘጋጀን ነበር።

69. አቶ ሙላቱ: (threatening) ከሷ ጋ እንደነበርሽ ትዕግስትን ብጠይቃት ይህን የምታረጋግጥልኝ ይመስልሻል?

70. ምህረት : በደንብ አባዬ። እመነኝ። አሁን የምትበላውን ላቅርብልህ።

71. አቶ ሙላቱ: (angry) ምንም የሚበላ ነገር በቤቱ የለም ምህረት። ከእንግዲህ በኋላ ዘግይተሽ እንዳትመጪ። ትሰሚኛለሽ?

72. ምህረት : አዎን አባዬ ይቅርታ።... ግን አባዬ...?አያቶቼ ቤት ሄጄ እናቴን ላገኛት እፈልጋለሁ።

73. አቶ ሙላቱ : ለምን? ከእኔ ጋ በመሆንሽ ደስተኛ አይደለሽም?

74. ምህረት : አይደለም አይደለም አባ። ሳልደሰት ቀርቼ ነው ማለት አይደለም። ግን እማዬ ናፍቃኛለች። ላናግራትም እፈልጋለሁ።

75. አቶ ሙላቱ : በምን ጉዳይ ላይ? ቀጥይ እየሰማሁኝ ነው።

76. ምህረት : ስለ ወደፊት ህይወቴ።

77. አቶ ሙላቱ : እና እናትሽ ብቻ ናት ስላንቺ የወደፊት ህይወት የበለጠ የምትነግርሽ? እኔ አይመለከተኝም ማለት ነው?

78. ምህረት : አይ አባዬ። ግን ለምንድን ነው ዘውትር እንደዚህ የሚሆነው? ለምንድን ነው ሁልጊዜከአንተ እና ከእሷ እንድንመርጥ የምትፈልገው?

**79.** አቶ ሙላቱ : መልካም እናትሽ ጋ መሄድ ትችያለሽ። ግን እዚያ እንዳታድሪ። ሀሳብሽን በነገር እንድትመርዘው አልፈልግም። ደግሞ የምትልሽን በሙሉ አንድ ሳታስቀሪ እንድትነግሪኝ እፈልጋለሁ። ግልፅ ነው?

**80.** ምህረት : አዎን ይገባኛል።

**81.** አቶ ሙላቱ : እዚያ ስትሄጂ በደንብ ተመልከቻት። ደስተኛ መሆን እና አለመሆኗን እንድትነግሪኝ።

**82.** ምህረት : **(politely)** እሺ ግን አባዬ…ለሚቀጥለው ሳምንት ለምሳዬ እና ለአውቶቢስ ቲኬት መግዣ ገንዘብ ትሰጠኛለህ?

**83.** አቶ ሙላቱ : ምንም ገንዘብ የለኝም።

**84.** ምህረት : እንግዲህ ምን ላደርግ ነው? ሰኞ ዕለት ፈተና አለን። ትምህርት ሊያመልጠኝ አይገባም።

**85.** አቶ ሙላቱ : እግሮች አሉሽ። አይደለም እንዴ?

**86.** ምህረት : ምግብስ? ለምግብ ከየት አመጣለሁ?

**87.** አቶ ሙላቱ : እኔም ራሴን እየጠየኩ ያለሁት ይሄንኑ ነው። መልሱን እንዳገኘሁ እነግርሻለሁ ምህረት ።

**88. MUSIC TRANSITION**

## <u>SCENE THREE: ንጉሴ STEALS HIS FATHER'S CAR KEYS</u>

**89. AMBIENCE: TV PLAYS IN BACKGROUBD**

**90. SFX: WHISKEY POURED INTO GLASS**

**91.** አቶ ጃለታ : **(sipping from glass)** እእም! ጣዕሙ ግሩም ነው። ከአድካሚ ስራ መልስ ምሽቱን ከተወዳጅ ባለቤቴ ጋ ሆኖ ውስኪን በበረዶ ከመጎንጨት የበለጠ ምን ግሩም ነገር አለ? **(laughs)** የሰማሁትን አንድ ዜና ለመንገር አሁን ጥሩ አጋጣሚ መሰለኝ የንጉሴ እናት ።

**92.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ምን አይነት ዜና ጃለታ ? ምንድን ነው?

**93.** አቶ ጃለታ : እስቲ ገምቺ? ሙላቱ እና ቤተሰቡ ከታንዲካ ጎስቋላ መንደር እንደለቀቁ ሰማሁ።

**94.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(shocked)** አላልኩህም? አውቄያለሁ። ከስርቆቱ ጀርባ እጁ መኖር አለበት። ካለዚያማ እኛጋ የዘበኝነቱን ስራ ትቶ እንደዚህ ለዛውም የተሻለ ህይወት ሊመራ ይችላል! ይህንን ለፖሊስ ማሳወቅ ይኖርብናል።

**95.** አቶ ጃለታ : የለም። አሁን አይደለማ። በቂ መረጃ የለንም። ወደ ተሻለ ቦታ መቀየር የምንም ነገር ማስረጃ ሊሆን አይችልም። ምናልባት ሙላቱ ሎተሪ ደርሶት ይሆናል።

**96.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ሎተሪ! እሱና እነዚያ መኪናዬን የሰረቁ ወሮበላዎች ወህኒ ሊገቡ ይገባል።

**97.** አቶ ጃለታ : ይገባሉ…ግን በሌላ ጥፋት ነው።…

**98. SFX:** አቶ ጃለታ **SIPS HIS DRINK**

**99.** አቶ ጃለታ : … ንጉሴ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ቀኑን ሙሉ እዛቹ ክፍሉ ተዘግቶ እኮ ነው የዋለው።

**100.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ምንም የማውቀው ነገር የለም። አያጠና ይሆናል።

**101.**አቶ ጃለታ : ምናልባት… አዎ ይሆናል።ቆይ ግን? ሽርሽር ወጥተን ብንመለስ ምን ይመስልሻል? የእዛች የሳምራዊት እናት ታማለች ሲሉ ነበር። ሄደን ብንጠይቃትስ? …

**102.**ወ/ሮ ዘውዲቱ: ውይ እሺ። መታመሟን አልሰማሁም ነበር።ቆይ ጫማዬን ላምጣ

**103.**አቶ ጃለታ : መጣሁ እኔም ላድርግ።

**104. SFX: FOOTSTEPS ON CARPET - TWO PEOPLE LEAVING**

**105. SFX: DOOR OPENING AND CLOSING**

**106. TENSE MUSIC**

**107. SFX: DOOR ON THE OTHER SIDE OF THE ROOM OPENS**

**108.**ንጉሴ : **(from this side of the room)** በጣም አሪፍ። ወላጆቼ በመኪና አይደለም የሄዱት። እንዴት አሪፍ ቀን ነው። መቼም እንደዚህ አይነት እድል ሌላ ቀን አይገጥመኝም።

**KW BEGIN**

**109. SFX: BUNCH OF KEYS BEING PICKED UP**

**110. SFX: HURRIED FOOTSTEPS**

**111. SFX: DOOR OPENING**

**112. OUTDOOR ATMO - SUBURB IN THE EVENING**

**113.**ንጉሴ: **(excited)** ቢንጎ! በጣም አሪፍ! እኔ ከዳንኤል እንደምሻል ለምህረት አሳያታለሁ። አንዴ በመኪና ከወሰድኳት ያንን ደደብ ትረሳዋለች።

**114. SFX: CAR ALARM BEEPS, UNLOCKING**

**115. SFX: CAR DOOR OPENING**

**116. SFX: CLOTH RUSTLE (ንጉሴ SITS DOWN)**

**117. SFX: CAR DOOR CLOSING**

**118. SFX: ንጉሴ BUCKLING UP**

**119. ንጉሴ :** ይህን ነበር ስል የነበረው።

**KW END**

**120. SFX: IGNITION KEY TURNING – CAR ENGINE STARTS AND REVS SEVERAL TIMES**

**121. ንጉሴ :** **(thrilled)** ያያያ አሁን መንገዱን ላይ መንካት ነው።

**122. SFX: RADIO ON, LOUD HIP-HOP MUSIC**

**123. SFX: CAR SKIDS AWAY AT FULL SPEED**

**124. MUSIC TRANSITION**

**125. <u>OUTRO- NARRATOR:</u>**

የንጉሤ ፍጥነት «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» በሚል ርዕስ የቀረበው የበማድመጥ መማር ድራማ 17ኛ ክፍል መደምደሚያ ላይ ያደርሰናል። ንጉሴ ምን ይገጥመው ይሆን?ያለ መንጃ ፍቃድ የአባቱን መኪና ሰርቆ እየነዳ ነው። ዳንኤልስ ለምህረት እምቢታ ምላሹ ምን ይሆን? መልሱን ለማግኘት ድረ ገፃችን dw.de/lbe ላይ ገብታችሁ የቪድዮ ዘገባውን ተመልከቱ። በፌስቡክ አድራሻችን ላይም እንዲሁ መከታተል ይቻላል። እስከሚቀጥለዉ ዝግጅት ድረስ ጤና ይስጥልን።